# ፖሊሲ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተጨማሪ የመረጃ ምንጭ:** ABA, ABC, ABC-RA, ACA, AEB, GEG-RA, IFA, IFA-RA, IHB-RA, IKA, IKA-RA, IOA, IOA-RA, IOB, IOD, IOD-RA, IQD, IQD-RB, ISB-RA, JEA-RA

**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፦** የአካዳሚ ዋና ኦፊሰር

# ስለ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ትምህርት

A. **ዓላማ**

የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ዓመታት የእያንዳንዱ ልጅ አካዴሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት የሚታነጹበት እና ለወደፊት ስኬታቸውም መሠረታዊና ወሳኝ ጊዜያት ናቸው። በመሆኑም የትምህርት ቦርድ ጠንካራ እና ሁሉን አቀፍ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ለማዘጋጀት ቁርጠኛ ሲሆን ይህም በመማር እና በማስተማር ላይ ቀጣይነት ያለው መሻሻል እንዲኖር መሰረት ይጥላል። እንዲህ ዓይነቱ ፕሮግራም ለሁሉም ተማሪዎች የአካዳሚክ ስኬት ከፍተኛ ተስፋ የሚሰጥ እና 6ኛ፣ 7ኛ፣ እና 8ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ እድገታቸውን የሚደግፉ ተግባሮችን ያካትታል።

መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በራስ የመተማመን፣ የብቃት እና የገለልተኛ የውሳኔ አሰጣጥ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ እና ተማሪዎች በአካዳሚክ እራሳቸውን ለመፈተን እና ፍላጎቶቻቸውን እንዲመረምሩ/እንዲቃኙ የሚደግፍ እድል ነው። በጠንካራ ሥርዓተ ትምህርት፣ ለወጣቶች በተዘጋጀ ትምህርት እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ተማሪዎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና የሥራ ዓለም ሽግግር ሲዘጋጁ ስኬታቸውን ከፍ ሊያደርግ ይችላል።

በእያንዳንዱ ልጅ የትምህርት ስኬት ውስጥ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ቤተሰቦች ቀዳሚ ባለድርሻዎች ናቸው፤ እና ቦርዱ ከወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ከቤተሰቦች እና ከማህበረሰቡ ጋር ያለውን አጋርነት እንደ አስፈላጊ የትምህርት ሂደት አካል አድርጎ ይመለከታል።በተለይም የማህበረሰቡን ብዝሃነት ከሚያንፀባርቁ ቡድኖች ጋር እንደዚህ አይነት ትብብሮችን ማሳደግ እና ዘላቂ እንዲሆን ማድረግ አካዳሚክ ስኬትን ለማስተዋወቅና እንዲሁም በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ዘመናቸው የተማሪዎችን አእምሯዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ እድገትን ለመደገፍ ውጤታማ መንገድ መሆኑን ይገነዘባል።

B. **ጉዳይ**

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ምረቃ መስፈርቶችን ለሚያሟላ ጠካራ አካዴሚያዊ፣ተገቢ እና ሁሉን አቀፍ እቅድ የሚያዘጋጁበት እና የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ግብ የሚንፀባረቅበት ሂደት ወሳኝ ወቅት ነው። ስለዚህ አጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርትን የሚያካትት የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መርሃ ግብር ጥብቅ፣ የተለየ የትምህርት ፕሮግራም፣ ከፍተኛ ብቃት ያለው እና ቁርጠኛ ሰራተኛ እና አመራር፣ የትብብር ግን እንደሁኔታው የተመቻቸ ድርጅታዊ መዋቅር፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ለእያንዳንዱ ተማሪ ስኬትን ለማረጋገጥ ለተሣተፈ ወላጅ እና ባለድርሻ ማህበረሰብ እድሎችን መፍጠር አስፈላጊ ነው። MCPS ይህንን አላማ ብዝሃነት ባለው ማህበረሰብ ውስጥ ከተለያዩ የትምህርት ፍላጎቶች ጋር ማሳካት አለበት።

C. **አቋም**

በጉርምስና/ኮረዳነት እድሜ ክልል የሚገኙ ተማሪዎችን ፍላጎት የሚያሟላ ጥብቅ የትምህርት ፕሮግራም ለመመስረት እና ለማቆየት የሚከተሉት መሰረታዊ ነገሮች አስፈላጊ ናቸው።

1. በትምህርት ቤት ያለው ባህል

   አእምሮአዊ እድገትን፣ ዜግነትን፣ ሃላፊነትን እና መከባበርን የሚያበረታታ ባህል ለማዳበር ትምህርት ቤቶች ከወላጆች/አሳዳጊዎች እና ከሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር በመተባበር የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለባቸው።

   a) ተማሪዎች የሚጠበቁበት፣ የሚበረታቱበት፣ እና በከፍተኛ ደረጃ እንዲማሩ እና እንዲሳካላቸው እድሎችን የሚሰጥበት አነቃቂ እና ደጋፊ አካባቢ መስጠት።

   b) ሁሉም ተማሪዎች አእምሯዊ ጠንካራ ኮርሶችን እንዲከታተሉ እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፉ አበረታቷቸው።

   c) በተማሪዎች መካከል እና በጎልማሶች እና ተማሪዎች መካከል አወንታዊ ግንኙነቶችን የሚያበረታታ በደንብ የሚተዳደር፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተንከባካቢ አካባቢን መጠበቅ።

   d) ከቦርድ ፖሊሲ ACA ጋር በማጣመር፣ ፀረ-አድሎአዊነት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት፣ በቦርድ ፖሊሲ ACA ውስጥ እንደተገለጸው የአንድን ግለሰብ ትክክለኛ ወይም በይሆናል ግላዊ ባህሪያትን ግምት ውስጥ ሳይገባ በተማሪዎች፣ በሰራተኞች እና በትምህርት ቤት ማህበረሰብ መካከል የባህል ብቃትን ማሳደግ።

   e) በማህበረሰቡ ውስጥ በሚነገሩ ቋንቋዎች፣ በተቻለ መጠን ከማህበረሰቡ ጋር ግንኙነትን ማመቻቸት።

   f) ትምህርትን በሚደግፉ ትርጉም ባላቸው መንገዶች ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እንዲሳተፉ ማድረግ፣ ለከፍተኛ የተማሪ ስኬት የረጅም ጊዜ የትምህርት እቅድ አስፈላጊነትን አፅንዖት መስጠት።

   g) ሁሉም ተማሪዎች ከሁሉም የትምህርት ፕሮግራሞች እና የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ፍትሃዊ እድሎችን ለመስጠት እና ለማረጋገጥ መስራት።

2. *ሥርዓተ ትምህርት፣ ማስተማር እና ግምገማ*

   MCPS የስርአተ ትምህርት፣ ማስተማር እና ግምገማ አቀራረብ ለሁሉም የመለስተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው ጠንካራ ትምህርት ማግኘታቸውን የሚያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ በጉርምስና/በኮረዳነት እድሜ የሚገኙ ተማሪዎችን ልዩ የትምህርት ፍላጎቶች ያሟላል። ቴክኖሎጂ የተማሪዎችን በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ ያላቸውን ፍላጎት እና ችሎታ ለመገንባት ወይም ለማጠናከር ከስርአተ ትምህርት፣ ማስተማር እና ግምገማ ጋር ይጣመራል።

   a) የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስርአተ ትምህርት ከቦርድ ፖሊሲ IFA፣ ስርአተ ትምህርት እና MCPS ደንብ IFA-RA፣ ስርአተ ትምህርት፣ እና የሚከተሉትን ጭምር ያካትታል፡-

      (1) በስርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ እና በስርዓተ-ትምህርት መመሪያዎች ውስጥ እንደቀረበው የተፃፈ ስርዓተ-ትምህርት።

(2) መምህራን ያስተማሩት ሥርዓተ ትምህርት በተማሪዎች ሲተገበር።

(3) የተማሩት ትምህርት በተማሪዎች ሥርዓተ-ትምህርት አፈጻጸም ግምገማ እንደታየው።

(4) ቀጣይነት ያለው አተገባበርን፣ ክትትልን እና ቁጥጥርን ለማረጋገጥ የሚያስፈልገው ሙያዊ እድገት።

(5) በሁሉም መምህራን፣ አስተዳዳሪዎች እና በማእከላዊ የአገልግሎት ሰራተኞች የስርአተ ትምህርት ትግበራን መከታተል።

b) የማስተማሪያ ልምዶች ተማሪዎች ንቁ እና ታታሪ ተማሪዎች እንዲሆኑ የሚያበረታታ እና የቦርድ ፖሊሲዎች IKA፣ የትምህርት ውጤት መስጠት እና ሪፖርት ማድረግን የመሳሰሉ የተለያዩ ዘዴዎችን፣ ስልቶችን እና ግብዓቶችን ያካትታል። IOA፣ ጎበዝ ተሰጥኦ እና ችሎታ ያላቸው ትምህርት፣ IOD፣ ለእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች ትምህርት፣ IOB፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርት እና MCPS ደንብ IHB- RA፣ በትምህርት ቤት የአካዳሚክ ቡድን ተግባራት።

(1) የፕሮግራም እና የማስተማር ውሳኔዎች ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በረዥም ጊዜ እቅድ የሚመሩ ስለሆነ በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው፤ ይህም የተማሪዎችን አካዳሚያዊ ፈታኝ አጠቃላይ እቅድ፣ የተማሪ እና የወላጅ/አሳዳጊ ፍላጎቶችን ጨምሮ፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ የተማሪ ተነሳሽነት፣ እና የተማሪ የትምህርት ክትትልና አፈጻጸም መረጃ ከተቀመጡት መመዘኛዎች አንጻር መተንተንና መገምገምን ይጠይቃል።

(2) ተማሪዎች የችሎታ ብቃታቸውን ለማሳየት እና የራሳቸውን አካዴሚያዊ ግስጋሴ ለመከታተል በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በጠቅላላ ቴክኖሎጂን ይጠቀማሉ።

(3) ተማሪዎች በአለም አቀፍ ማህበረሰብ ውስጥ እንዲሰሩ እና እንዲወዳደሩ ለማስቻል እና በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ቴክኖሎጂን መጠቀም እንዲችሉ ለማብቃት በተለይም የማህበረሰቡን ብዝሃነት የሚያንፀባርቁ ሁሉም ተማሪዎች በቴክኖሎጂ ትምህርት ማግኘት አለባቸው።

(4) የተለያዩ የማስተማር ተግባሮች ፈጣን፣ የተማሪን አፈጻጸም ለማሻሻል ድጋፍ የሚሰጥ፣ የሚያበለጽግ፣ እና ሌሎች ስልቶችን እንደ አስፈላጊነቱ የአእምሮ እድገትን ለማጎልበት እና ተማሪዎች የአካዳሚክ አቅማቸውን እንዲያዳብሩ ይረዷቸዋል። እንዲህ ዓይነት ተሞክሮዎች በተማሪዎች መካከል የመማር ዘዴዎችን እና የአካል፣ ማህበራዊ፣ እና ስሜታዊ ልዩነቶችን ይፈታል።

(5) በሁለቱም የትምህርት አሰጣጥ ስልት፣ እቅድ፣ እና አተገባበር፣ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሁሉም አጠቃላይ፣ አማራጭ፣ የሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች (ESOL) እና የልዩ ትምህርት ሰራተኞች አባላት ልዩ ችሎታዎችን ይጠቀማሉ።

(6) የማስተማር ተግባሮች ለተማሪዎች የመሪነት እድሎችን መስጠትና እንዲሁም የተማሪ ንግግርን እና ራስን የመግለጽን ውጤታማነት ማሳደግ አለባቸው።

(7) የተማሪ አገልግሎት ትምህርት መስፈርቶች ተማሪዎች በማህበረሰቡ እና በሌሎች ከትምህርት ቤቶች ድባብ ውጪ የተለዩ አካባቢዎች ላይ ትምህርት እንዲቀስሙ እድል ይሰጣቸዋል።

c) የግምገማ ተግባሮች፣ በቦርድ ፖሊሲ IKA ላይ እንደተብራራው፣ የትምህርት ውጤት መስጠት እና ሪፖርት ማድረግ፣የማስተማር ዑደቱ አስፈላጊ ገጽታ ስለሆኑ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

(1) ቅድመ-ግምገማዎች እና ፎርማቲቭ ምዘናዎች፣እንዲሁም የማጠቃለያ ምዘናዎች፣የግኝት ደረጃዎችን ለተማሪዎች ለማስተላለፍ፣የትምህርት ግቦችን ለማሳካት እቅድ በማውጣት እና በማድረስ፣በአፈፃፀማቸው ላይ ወቅታዊ ምላሽ ለተማሪዎች ይሰጣሉ፣እና ተማሪዎች እንዲማሩ ተጨማሪ እድሎችን ይሰጣሉ።

(2) ከካውንቲ፣ ከስቴት እና ከሀገር አቀፍ ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ አጠቃላይ የግምገማ ፕሮግራም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

(a) በጊዜ ሂደት በተለያዩ ልኬቶች ላይ የተማሪውን የአፈጻጸም ውጤት ፍትሃዊነት ማረጋገጥ።

(b) የተለያዩ ስልቶችንና ዘዴዎችን በመጠቀም መምህራን በጊዜ ሂደት የሚሰበሰቡት የተማሪ ትምህርት ማስረጃዎች።

(c) ለተማሪዎች፣ለወላጆች/አሳዳጊዎች፣ለመምህራን፣ ለአስተዳዳሪዎች እና ለትምህርት ስርዓቱ በተማሪ ስኬት ላይ ትርጉም ያለው አስተያየትና ግብረመልስ።

(d) የውጤት መስፈርቱን በሚመለከት ከወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተማሪዎች ጋር ግልጽ እና ወቅታዊ ግንኙነት ማድረግ።

(e) ትምህርት ቤቶች በተናጠል እና በትምህርት ቤቶች መካከል ወጥነትን ማረጋገጥ።

(3) እንደገና ማስተማር እና መገምገም መማርን የሚያበረታታ የጠንካራ የማስተማር ዑደት ዋነኛ አካል ናቸው። የድጋሚ ግምገማ ሂደቶች ፍትሃዊ ናቸው፣ ውጤታማ የመማር ማስተማር ጥረትን ያበረታታሉ፣ እና በማስተማር ሂደት ውስጥ የተካተቱ ናቸው።

3. ድርጅታዊ መዋቅር

ድርጅታዊ መዋቅሮቹ የተነደፉት፥ ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ለማሳደግ እና መልካም የትምህርት አሠጣጣቸውን ለማጎልበት የትምህርት ጊዜን ለማመቻቸት እና በተማሪዎች፣ በሰራተኞች፣ በወላጆች/አሳዳጊዎች እና በማህበረሰብ አባላት መካከል አወንታዊ ግንኙነቶችን ለመፍጠር እና የተማሪ ሽግግርን፣ ምደባን እና የፕሮግራም ቀጣይነትን በየደረጃው ለማመቻቸት ነው። ውጤታማ፣ እንደሁኔታው የተመቻቹ እና የተሳለጡ ድርጅታዊ መዋቅሮች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

a) በየክፍል ደረጃው ለሚገኙ የመምህራን ቡድኖች፣ የትምህርት ዘርፎች፣ እና በተመረጡ ኮርሶች መካከል የተሣለጡ እድሎችን መፍጠር።

b) ስለ ተማሪ በትምህርት ላይ የሚያሳየውን/የምታሳየውን እድገት ለመወያየት ሰራተኞች ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር የሚገናኙበት እድሎችን መፍጠር።

c) የጣልቃ ገብነት እና የማበልጸግ ፕሮግራሞች እንዲሁም በፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የምርጫ

ኮርሶች።

d) ልዩ የትምህርት ክፍሎችን እና/ወይም የተሻሻሉ የትምህርት እድሎችን ለመደገፍ መርሃ ግብሮችን እንደገና የማዋቀር ችሎታ።

e) አነስተኛ የሚማሩ ማህበረሰቦችን።

f) ሁሉን አቀፍ ወጥነትና ግልፅነት ያላቸው ዕቅዶች።

4. የተራዘሙ የትምህርት እድሎች

መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን ደረጃዎች እንዲያሟሉ እና የተፋጠኑ የትምህርት እድሎችን በሚሰጡ የአካዳሚክ መርሃ ግብሮች የተቀናጀ የትምህርት ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ። እንደዚህ አይነት ፕሮግራሞች በተማሪዎች እና በሰራተኞች መካከል ባሉ አወንታዊ ግንኙነቶች ላይ የተገነቡ እና ተማሪዎችን በሚያሳትፍ እና የተለያዩ ተማሪዎችን ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ መቅረብ አለባቸው።

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአካዳሚክ የተራዘመ የመማር እድሎች ከስርአተ ትምህርቱ ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው፥ እና ተማሪዎች ከክፍል ደረጃ ወይም ከክፍላቸው ደረጃ በላይ የሚጠበቁትን እንዲያሟሉ ወይም እንዲበልጡ መርዳት አለባቸው።

በተጨማሪም፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች በቦርድ ፖሊሲ IQD ድንጋጌ መሠረት፥ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ ተግባራት የአካዳሚክ ብቁነት እና MCPS ደንብ IQD-RB፣ በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚሳተፉ ተማሪዎች የአካዳሚክ ብቁነት መመሪያ መሰረት ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍ ፍላጎቶቻቸውን እንዲፈትሹ ለተማሪዎቻቸው እድሎችን መስጠት አለባቸው። እነዚህ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች፤ ለምሳሌ፥ በኪነጥበብ ውስጥ መሳተፍ፣የውድድር እና ተወዳዳሪ ያልሆኑ አትሌቲክስ እና ሌሎች ክለቦች የተማሪዎችን ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገት ስለሚያሳድጉ በትምህርት ቤት የተሟላ ተሳትፎን ያበረታታሉ።

5. አመራር እና ሙያዊ እድገት

MCPS የሙያ እድገት ሲስተም ለሁሉም አስተዳዳሪዎች፣ ለመምህራን እና የድጋፍ አገልግሎት ሰራተኞች እውቀታቸውን፣ ክህሎቶቻቸውን እና አቅማቸውን እንዲያሳድጉ የመማር እና የማስተማር ሂደቱን ያለማቋረጥ ለማሻሻል መደበኛ እና ስልታዊ እድሎችን ያካትታል። ዋና ጽሕፈት ቤት የሚከተሉትን በትምህርት ቤት ደረጃ መመስረት ያለባቸውን ሂደቶች ይደግፋል፡-

a) የትምህርት ቤቱን ወይም የትምህርት ክፍሉን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግቦች እና የድርጊት መርሃ ግብሮችን መከታተል እና ማሣለጥ።

b) ራዕይን ለመፍጠር እና ቀጣይነት ባለው መሻሻል ላይ ያተኮረ ከፍተኛ አፈፃፀም ያለው ድርጅትን የሚደግፉ ስልቶችን ለመተግበር ከባለድርሻ አካላት ጋር መስራት።

c) የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሻሻል በተነደፉ ሙያዊ እድገት እድሎች ላይ ሊሳተፉ የሚችሉ መሪዎችን መለየት።

d) የትምህርት ቤት ሰራተኞች ራዕያቸውን፣ ግቦቹን እና የድርጊት መርሃ ግብሮቹን ለማሟላት ያላቸውን አቅም የሚያጠናክሩ እና ለሁሉም ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቁ ነገሮችን የሚያጠናክሩ ውስጣዊ አቅምን መገንባት።

e) የተማሪን ውጤታማነት ለማሳደግ ከሁሉም ወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ለመግባባት እና ለማሳተፍ ውጤታማ ስልቶችን ለት/ቤት ሰራተኞች ሙያዊ እድገት መስጠት።

f) የትምህርት ቤት ሰራተኞች የይዘት፣ የክህሎት፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ ልዩነት እና የትምህርት አሰጣጥ እውቀታቸውን እንዲያሳድጉ ሙያዊ እድገትን መስጠት።

6. የወላጅ/አሳዳጊ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ግንኙነት

የቦርድ ፖሊሲ ABA መሠረት ያደረገ፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ፖሊሲ ABC፣ የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ፣ እና MCPS ደንብ ABC-RA፣ የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የማህበረሰብ አባላት በተማሪዎች ማህበራዊ እና አእምሯዊ እድገት ውስጥ ወሳኝ አጋሮች ናቸው። ይህ ትብብር የሚከተለው ጥቅም ይኖረዋል፡-

a) ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ቤተሰቦች የልጆቻቸውን አካዴሚያዊ ስኬት የመደገፍ አቅማቸውን የሚያሳድጉበት እድሎችን ይፈጥራል።

b) የአካዳሚክ፣የማህበራዊ እና የትብብር ፕሮግራሞችን በተመለከተ ለወላጆች/አሳዳጊዎች ግብአት፣ አስተያየት እና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተሳትፎ የማድረግ እድሎችን ይሰጣል።

c) መረጃን ለመስጠት እና በግለሰብ የልጆችን ትምህርታዊ እድገት እንዲሁም የአካባቢ እና የትምህርት ስርአቱን ፖሊሲዎች፣ ደንቦችን እና ተግባራትን በሚመለከት በማንኛውም ጊዜ በተቻለ መጠን በማህበረሰብ ውስጥ በሚነገሩ ቋንቋዎች በቤተሰቦች እና በት/ቤቶች መካከል ተደጋጋሚ የሁለትዮሽ የጋራ ግንኙነት ማድረግ።

d) ቤተሰቦች እና የማህበረሰብ አባላት በተማሪ እና በት/ቤት ፕሮጀክቶች፣ እንቅስቃሴዎች እና ዝግጅቶች ላይ እንዲሳተፉ የተለያዩ እድሎችን መስጠት።

e) የተማሪን ስኬት እና የወላጅ/አሳዳጊ ተሳትፎን ለመደገፍ ከአካባቢው የንግድ ማህበረሰቦች፣ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ሌሎች ኤጀንሲዎች እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነቶች ማድረግ።

7. ሰብአዊ ሪሶርሶች

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ሰራተኞች የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት የሚያስፈልገውን ክህሎት፣ ችሎታ፣ እና ይዘት እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ወሳኝ ነው። ከፍተኛ ብቃት ያላቸውን የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራንን የመቅጠር፣ የመሳብ እና የማቆየት ልምምዶች አካዴሚያዊ አፈጻጸምን እና የትምህርት ቤቶችን የተናጠል ፍላጎቶችን ለማሟላት መተግበር አለበት። እንደነዚህ ያሉ ፍላጎቶች የነጻ እና የቅናሽ ዋጋ የምግብ አገልግሎት ስርዓት ተሳትፎን፣እንቅስቃሴን፣አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰኑም።

በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሰራተኞች የሚከተሉትን ያደርጋሉ፡-

a) በመሠረታዊ የትምህርት ዓይነቶች ከፍተኛ ብቃት መቀዳጀት እና የትምህርት ይዘትን በውጤታማ የማስተማሪያ ዘዴዎች ማቅረብ መቻል።

b) ለሁሉም ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቅባቸውን ነገሮች ማስገንዘብ።

c) ለሙያዊ ትምህርት ማህበረሰቦች ማስተማር እና መማርን ለማሻሻል እድሎችን መፍጠር።

d) ስለ ጉርምስና/ኮረዳነት እድገት ባህሪያት ግንዛቤ መጨበጥ እና ሁሉም ተማሪዎች ሊማሩት የሚገባቸው ፅንሰ-ሃሳብ ላይ እውቀት ማግኘት።

e) ከተማሪዎች ጋር በመማር ሂደት ውስጥ የሚያሳትፏቸውን ግንኙነቶች መፍጠር።

f) የትምህርት ሂደቱን ለመደገፍ በወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሰራተኞች መካከል ግንኙነቶችን ማዳበር።

g) በተቻለ መጠን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) የህዝብ ብዝሃነት ማንፀባረቅ።

D. ***ተፈላጊ ውጤቶች***

1. የአካዳሚክ ስኬትን የሚያጎላ ትምህርታዊ ፕሮግራም።

2. በሁሉም የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ውስጥ የተዋሃዱ እና ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ የሆኑ ዋና ርዕሰ ጉዳዮች፣ የተመረጡ ኮርሶች እና የልዩ ፍላጎት እንቅስቃሴዎች ይኖራሉ።

3. ተማሪዎችን በተሳካ ሁኔታ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና የስራ አለም እንዲሸጋገሩ የሚያዘጋጇቸው ፕሮግራሞች፣ ኮርሶች፣ እንቅስቃሴዎች እና የትምህርት ልምዶች።

4. በመካከለኛ ደረጃ ትምህርታቸው ከተማሪዎች፣ ከሰራተኞች፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች እና የአካዳሚክ ስኬትን ከሚደግፉ እና ከሚያበረታቱ ቤተሰቦች እና ተማሪዎች ጋር ምሁራዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ እድገት ማዳበር።

5. የእውቀት እድገትን የሚያበረታታ ባህል፣ እንዲሁም ዜግነትን፣ ሃላፊነትን እና በተማሪዎች መካከል መከባበርን እንዲሰፍን ማድረግ።

E. ***ግምገማ-ክትትል እና ሪፖርት***

ይህ ደንብ በቦርድ የማሻሻያ መመርያ መሰረት ክለሳ ይደረጋል።

**የፖሊሲው ታሪክ፡-** በውሳኔ ቁጥር 486-92፣ ጁን 22, 1992 ተደነገገ፤ በውሳኔ ቁጥር 98-07 ፌብሩወሪ 26, 2007 ተሻሽሏል፣ ቴክኒካዊ ማሻሻያዎች በውሳኔ ቁጥር 319-17 ጁን 26, 2017 ተደርጓል።

**ማሳሰቢያ፡-** ከውሳኔ ቁጥር 486-92 በፊት፣ ይህ ድንጋጌ የሚከተለው ነበር፡ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፖሊሲ፣ በውሳኔ ቁጥር 827-77፣ ዲሴምበር 13፣ 1977 የጸደቀ። በውሳኔ ቁጥር 333-86 ጁን 12 ቀን 1986 እና ውሳኔ ቁጥር 458-86 ኦገስት 12 ቀን 1986 ተሻሽሏል። በውሳኔ ቁጥር 347-88 ጁን 27 ቀን 1988 ተሽሯል። የጁኒየር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፖሊሲ፣ በውሳኔ ቁጥር 163-74፣ ማርች 25፣ 1974 የጸደቀ። በዲሴምበር 13, 1977 ውሳኔ ቁጥር 827-77 የተሻሻለው። በውሳኔ ቁጥር 333-86 ጁን 12 ቀን 1986 እና ውሳኔ ቁጥር 458-86 ኦገስት 12 ቀን 1986 ተሻሽሏል። በውሳኔ ቁጥር 347-88 ጁን 27 ቀን 1988 ተሽሯል። በውሳኔ ቁጥር 347-88 ጁን 27 ቀን 1988 የፀደቀ አዲስ ፖሊሲ፣ በውሳኔ ቁጥር 486-92 ጁን 22 ቀን 1992 ተሽሯል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ጁን 2022